# <u>የጣና ሐይቅም ይደርቃል የጢስ እሳት ፏፏቴ ተሰርቋል</u>

በአለፉት ጊዜያት ስለ ጢስ አባይ ፏፏቴ መድረቅና የጣና ሐይቅም ለከፈተኛ ሥነ ምኅዳራዊ አደጋ መጋለጥ ጽፌ ነበር። ጽሑፉን ለንባብ ያበቁት ጥልቅ ምስጋና ይድረሳቸውና ጥቂት ድህረ ገጾች ብቻም ነበሩ። ነገር ግን በአባይ ፏፏቴ ፎቶ ግራፍ ከወያኔ ፕሮፓጋንዳ ነዥዎች ጀምሮ በአገር ቤትና በባሕር ማዶ የሚገኙት የአበሻ ምግቤቶችና ድርጅቶች ሁሉ ያልተዋባ የለም። ይህም ሆኖ ያባይ ፏፏቴ መድረቅ ለኢትዮጵያዊ ተብዬ ፖለቲከኞች፣ ምሁራኖች፣ ነጻ አውጪ ተባይ ግንባሮች፣ የወሬ አርበኖች ወዘተረፈ ሁሉ በጭራሽ የሚያሳስባቸው ጉዳይ ያለመሆኑን ተገንዥቤአለሁ።

የወያኔ ትግሬ ኢሕአዴግ መንግሥት ተብዬው በሰሜን አፍሪቃ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመጽ ስለ አሰበረገገው በድንገት በአባይ ወንዝ ሱዳን ጠረፍ ላይ ታላቅ ግድብ እገነባለሁ ብሎ እንደተለመደው ለብቸኛ ደንበኛው ለጣሊያን ሳሊኒ ግንባታ (Salini Constriori of Italya) ለተሰኘው ድርጅት ያለምንም ጭያረታ መስጠቱ የታወቀ ነው። የግድቡ ግንባታ ዕቅድ የመሠረቱ ድንጋይ ተተከለ ተብሎ ቡራ ከረዩው በሰፊው ተነዛ። ከሁለት ዓመታት በኋላ በግንቦት ሃያ ቀን ደግሞ ያባይ ወንዝ የፍሰት አቅጣጭያን ቀየርን በማለት የተነዛውን ፕሮፓጋንዳ አስመልክቶ ከግብፅ ጋራ አተካሮ ተጀመረ። ወጡ ሳይወጠወፕ የወስከምባው መሮጥ እንዲሉ ወያኔ ኢሕአደግ በአባይ ላይ ታላቅ የሕዳሴ ግድብ ለመገንባት ጀምሬአለሁ እያለ ተደናብሮ ያደናብራል። ሕዝቡ በኑሮ ውድነት የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ እግዚኦ ይላል። በቡሃ ላይ ቆረቆር ሆነና ለእለት ኑሮ እንኳ የሚሆን የሌላቸውን ፍጹም ምስኪን ድሃ ገበሬዎችንና ሠራተኞችን ገንዘብ አዋጡ፣ የወር ደሞዛችሁን በዓመት ክፈሉ፣ ቦንድ ግዙ እየተባሉ ቁምስቅላቸውን ያያሉ። በአንጻሩ የወያኔ ሽማምንት አሥራ አንድ ቢሊዎን የአሜሪካ ዶላር በወጭ አገር ባንክ ገቢ ማድረጋቸውን ምዕራባውያኑ መስክረዋል። በመለሰ ዜናዊ ሂሳብ ቁጥር ከሦስት ቢሊዎን ያሜሪካ ዶላር ከኢትዮጵያ መዘረፉን፣ ሁሉም የወያኔ ሽማምንትና ካድሬዎች በሙስና መዘፈቃቸውን ዓለም ያውቀዋል።

የግድቡ ዋና ዓላማ 5250 ሜጋዋት የኮረንቲ ኃይል ለማፍለቅና ለውጭ አቅርቦት ለማቅረብ ብቻ ነው። ከዚሁ ጋራ ተያይዞ ለግድቡ ግንባታ መዋዕለ ንዋይ ግብጾችና ሱዳኖች ከሠላሣ እስከ አርባ በመቶ እጅ ተካፋይ እንዲሆኑ ወያኔው ጥሪ ማድረጉንና፣ ግብጾች ለአቀረቡት ጥያቄ ሁሉ መስማማቱን ሰምተናል። ታዲያ ሁኔታው እንዲ ሆኖ ሳለ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶችና ግለሰቦች የግድቡን ግንባታ አስመልክተው የሚያደርጉትን ተገቢ ተቃውሞ ወያኔና ጀሌዎቹ ሁሉ በፀረ ኢትዮጵያዊነት ፈርጀው ያቅራራሉ።

ነገሩስ ጨቋቴን ቀሙኝ ነው። መቼም ኢትዮጵያ በታሪኳ እንደ ወያኔ ኢሕአዴግ ያለ ፀረ ኢትዮጵያ መንግሥት ተብዬ አፉኝ ፈላጭ ቆራጭ አረመኔ የባንዳዎች ጥርቃሞ ድርጅት በታሪክ ብጭራሽ አገጥሚት አያውቅም። በመሆኑም ወያኔ ኢሕአዴግ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ልዑላዊነት፣ እድገትና ልማት ይቆማል ማለት ወሃ በተፈጥሮ ሽቅብ ይፈሳል ብሎ ከንቱ ምኞት፣ ጨረቃ ዳቦ ጣይ ይሆናል። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአባይ ወንዝ ላይ ግድብ መገንባትን ከቶ አይቃወምም። ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የኤሌክትሪክ ጉልበት የሚጠቀመው ሕዝብ ብዛት 12 ከመቶ እጅ ብቻ በሆነበት፣ በዘመን ወያኔ የአፍሪቃ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ እንኳ ሳይቀር ኮረንቲ በፈረቃ በሚታደልበት፣ ከውሃ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ጉልበት የማፍለቅ ችሎታዋ እጅግ ባጣም ከፍተኛ ከሆኑት የዓለም አገሮች እንዷ ሆና ለአፍሪቃ፣ ለአረቢያና ደቡብ አውሮፓ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ ብቃት እንዳላት የተረጋገጠ መሆኑ እየታወቅ የኃይል ማመንጭያ ግንባታ አይደርግ ብሎ የሚቃወም የለም። ዋናው ጥያቄ ግን ስለ ግንባታው የሚነሱት ሙያዊ፤ ኢኮኖሚያዊ መልካ ምድራዊ፣ የግድቡ ደህንነት የመሳሰሉትን ሃሳቦች በጥልቅና በስፋት ማገንዘብ ግድ ይላል።

ወያኔ ኢሕአዴግ በአለፉት ዓመታት ያለምንም ሥነ ምኅዳራዊና አካባቢያዊ ጥናት፣ ያባይን ፏፏቴ አድርቋል። የጣና ሕይቅን በመሸንቆር ውሃን በጠቅላላ ወደ በለስ ወንዝ እንዲፈስ በማድረግ ለድርቀት አመቻችቷል። ያለ ምንም ጥናትና ዝግጅት በድንገት ሱዳን ጠረፍ ላይ ታላቅ ሕዳሴ ግድብ ለመገንባት ጀመርኩ እያለ ይወሻክታል። የኢትዮጵያ ከተሞች በጭለማ ተውጠው የኮረንቲ ኃይል ለኬኒያ፣ ለሱዳንና ለጅቡቲ እናቀርባለን እየተባለም በጣም በሰፊው ይቦተለካል።
እንዲሁም ዘወትር ተቆራርጦ የሚቀርበው የኮረንቲ መብራት ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ ጣራ ደርሷል። በዚህም ሳቢያ በኢትዮጵያ የከተማው ሆነ የገጠሩ ሕዝብ ለምግብ ማብሰያ የሚጠመቀው የዕንጨት ማገዶና ከሰል ብቻ ሆኖ ቀጥሏል። ሌላ ምንም አማራጭ ስለሌለው በያለበት ዕንጨት እየተመነጠረ ደኑ ተራቆቷል። ይህም ከፍተኛ የአካባቢ ቀውስ፤ ተከታታይ ድርቅና የዐፈር መጠረግን አስከትሏል። ወያኔ የልማት መንግሥት ነኝ እያለ ጠዋት ማታ ይለፍፋል።
ነገር ግን ብዙኃኑ አርሶ አደር በቁራጭ መሬት ተወስኖ በደርግ ኮምኒስቲ ተብዬ ርስቱን ተቀምቶ መቆየቱ ሳያንሰው ዛሬም የወያኔ ቅጥረኛ መንግሥት ተብዬው ጭሰኛ ሆኖ የግል ባለንብረትነት መብቱን ተነፍጓል። ይባስ ተብሎም በምዕራብና መሃል አገር ይልቁንም በጋምቤላና መተከል በጎንደር፣ በጎጃም፤ በሸዋ እጅግ ሰፋፊና ለም መሬቶችን፤ የተፈጥሮ ደኖችም ጭምር ሳይቀሩ ለውጪ ከበርቴዎች በገፍና በርካሽ ዋጋ በመሸጥ ላይ ናቸው። በዘመነ ደርግ በድርቅ የተጎዱትን የሰሜን ኢትዮጵያ ገበሬዎች በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ ሰፍረው የነበሩትን ገበሬዎች በኀሣ ማጽዳት ተባረው ሰፋፊው ለም መሬትና ደን ለውጪ የአረብ፣ የሕንድና አውሮፓ ከበርቴዎች በርካሽ ለብዙ ዓመታት ተሸጠዋል።

## የጣና በለስ ኃይል ማመንጭያ ጣስ

የጣና ሐይቅ በኢትዮጵያ ትልቁ የሐሩር አውራጃ ንፁሕ ውሃ ሐይቅ፣ የአባይ ወንዝ መጋቢ፣ በውስጡ 37 ደሴቶችን ይዞ የብርቅዬ ዕፅዋትና እንስሳት ምችጌ መኖሪያ፣ ጥንታዊ የኦርቶዶክስ ክርስትና ገዳማት ያሉበት፤ የታሪክና ባሕል ቅርሶች ግምጃ ቤት ነው።
በጣና ሐይቅ ውስጥ 65 የዓሣ ብቸኛ ዘርያዎች እንዲሁም ከሁለት መቶ በላይ አእዋፋት ዓይነት አሉት። ከሐይቁ 35 ኪሎሜትር ርቀት ደቡብ ምሥራቅ ላይ የተፈጥሮ ውብ አስደናቂው ፏፏቴ አገር ጎብኝዎችን ሳቢው እስከ 45 ማትር ያህል ከፍታ ያለው <u>የጢስ እሳት ፏፏቴ ይገኝ ነበር።</u> የአባይ ወንዝ ፏፏቴውን አልፎ በጥልቅ ሸለቆው ውስጥ እየፈሰሰ ምሥራቃዊ አቅጣጭያውን ወደ ምዕራብ በኩል በመቀየር ወደ ሱዳን ይነጉዳል። የጣና ሐይቅ ርዝመቱ 85 ኪሎሜትር፣ ውርዱ 70 ኪሎሜትር ሲሆን አማካይ ጥልቀቱም 9 ሜትር ያህል ሲሆን ጠቅላላ ይዘቱም 28 ቢሊዮን ኩባዊ ሜትር፣ ስፋቱም 3672 ካሬ ኪሎሜትር ነው። የጣና ሐይቅ መጋቢ ዋና ወንዞች አራት ናቸው። እነዚህም ግልገል አባይ፣ ረብ፣ ጉመራና መገጭ ናቸው። እንዲሁም በሐይቁ ስፋት ላይ በክረምት ወራት በሚዘንመው ዝናም መጠን ይሞላል። የጣና ሐይቅ ጥልቀት በአለፉት 400 ዓመታት ውስጥ እየቀነሰ መምጣቱና ለአየር ንብረት መለዋወጥ በከፍተኛ ደረጃ የተጋለጠ መሆኑ ይታወቃል። የሐይቁ የውሃ ከፍታ መጠን ሊጢስ እሳት ሁለተኛ ኃይል ማመምንጭያ በመፋሰሻው ላይ በ1989 ዓ.ም በተገነባው ማገጃ (የጭያራ ጭያራ ግድብ Chara Chara weir) አማካይነት ይስተካከል።
የጣና ሐይቅ እስከ ጥቂት ዓመታት ድረስ እንደ ሌሎቹ የአፍሪቃና ሌሎች አህጉራት ሐይቆች ለምሳሌ ቪክቶሪያ ሐይቅ (ዩከረዊ)፣ የቻድ ሐይቅ ወዘተረፈ በሰው ሠራሽ ብክለትና የአካባቢ ጠንቆች ያልተበከለ፣ የሥነ ምኅዳር ሚዛኑ ያልተቃወሰ ነበር። የምሥራቅ አፍሪቃው ትልቁ ቪክቶሪያ ሐይቅ ጥልቀቱ በሜትር ተኩል ያህል ቀንሷል፣ ስፋቱም በከፍተኛ ፍጥነት እየቀነሰ በመሄድ ላይ ይገኛል።

ከዚህም ሌላ የአውሮፓ ቤልጅግ ቅኝገዥ ሰፋሪዎች በሩዋንዳ ከአሜሪካ አህጉር ያመጡት መጥፎ የውሃ አረም (*Echhiomia Crassipes*) ወደ ቪክቶሪያ ሐይቅ ተዛምቶ በጣም ከፍተኛ ያካባቢ ብክለት ማስከተሉ ይታወቃል። የቻድ ሐይቅ በብዛት ለመስኖ መዋሉና የአካባቢው ዕፅዋት በገፍ በመመንጠሩ ሳቢያ በደለል ተሞልቶ ስፋቱ ከ25 ሺህ ካሬ ኪሎ ሜትር ወደ ሺህ ሦስት መቶ ሃምሳ ካሬ ኪሎ ሜትር ቀንሷል። በቀድሞዋ የሶቪየት ሕብረት የአራል ሐይቅ የደረሰበትን ሰው ሠራሽ ከፍተኛ አደጋ ይገነዘቧል። በአገራችን የአለማያ ሐይቅ ድርቋል። የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች እንደ ዝ.ይ፣ አቢያታ፣ ሻላ ወዘተረፈ በደለል እየተሞሉ ነው።
ከጣና ሐይቅ ለበለስ ኃይል ማመንጭያ 9.14 ቢሊዎን ኩባዊ ሜትር ውሃ ማለትም ሲሰው ተወስዶለት ይቅርና በበጋ ወራት ጥልቀቱ እየቀነሰ የመርከብና ጀልባ መጓጓዣ ችግር መከሰቱ ይታወቃል። የጣና ሐይቅ አነስተኛ ጥልቀት ያለው ስለሆነ ለበለስ የሚወሰደው ውሃ መጠን አጠቃላይ ሥነ ውሃዊና ምኅዳራዊ ቀውስ  እንዳስከተለ ሳይታለም የተፈታ ነው።
በጥልቀቱ መቀነስ የደሴቶች አየር ንብረት ይቀያየራል፣ ሐይቁ የአባይ ወንዝ የተፈጥሮ ጋን መሆኑ አክትሟል። የሐይቁ ሁኔታ ለአየር ንብረት መለዋወጥ በከፍተኛ ደረጃ የተጋለጠ መሆኑ በግልፅ እየታወቀ ተፈጥሮ የሠራውን ግድብ ነድሎ ውሃውን በገፍ መውሰድ ዋና <u>የጠላት ሥራ እንጂ ከቶ ልማት አይደለም።</u>
የተፈጸመው ድርጊት ከዚህ ቀደም በአጤው ዘመነ መንግሥት የአባይ ወንዝ ሸለቆን ያጠኑት ያሜሪካ መሐንዲሶች እቅድና ሃሳብን በፍጹም ይፃረራል።

# <u>የወያኔ ሕዳሴ ተብዬ ግድብ የወለፌንድ ሥራ ነው</u>

ስለምንድን ነው ሱዳን ጠረፍ ላይ ለኮረንቲ ኃይል ብቻ ግድብ ለመገንባት የተፈለገውና የተወሰነው? ከመሃል አገር ይልቅ ጥልቅ ሸለቆ በጠረፉ ላይ ስለአለ የጠረፉ ግድብ የጣና ሐይቅን እጥፍ ያህል ውሃ ማለትም 62 ቢሊዎን ኩባዊ ሜተር ያህል ማጠራቀም ይቻላል ተብሎ የሚራገበው ፍጹም የፈጠራ ወሬ ነው። እንደሚታወቀው የጠረፉ አካባቢ በተፈጥሮ ዝቅተኛ ቆላማ የቀን አማካይ ልክ ሙቀት ከአርባ ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የሚደርስ በመሆኑ የሚከማቸው ውሃ በትነት ይባክናል።
የጣና ሐይቅን ውሃ መጠን ያህል መከተር የሚቻለው በከራዶቢ መሐል አገር ጉደር ወንዝ አጠገብ ብቻ እንደሆነ አሜሪካውያን መሐንዲሶች ያደረጉት ጥናቱ ያስረዳል።
በአለፉት ዓመታት የወያኔ የጎሣ ምልምሎች በኢትዮጵያ ውስጥ ከአባይ ወንዝ ሌላ የሌለ ይመስል በጣና ሐይቅና በጢስ አባይ ላይ ብቻ በተዘበራረቀና ጥቅመቢስ ጥናትና እቅድ ለጢስ እሳት ፪ኛ ና ለጣና በለስ የፈሰሰው ሰባት ቢሊዎን ብር በሌላ ተስማሚ ቦታዎች ለምሳሌ በዝማ፣ በበሽሎ፣ በጉደር፣ በዋቢሸበሌ፣ በከሰም፣ በቦርከና፣ በአዋዲ፣ በጎጀብ፣ በአንገረብ፣ በሞፈር ውሃ፣ በቀበና፣ በአዋሽ ወዘተረፈ እንዲሁም በአባይ ወንዝ ከፏፏቴ በታች ባሉት አመቺ መገደቢያ ጥልቅ አለትማ ሸለቆዎች ላይ ያስገነባ ነበር። የወያኔዎችና ባሕር ማዶ ቀጣሪዎቻቸው ፍጹም ቅዠታዊ ምኞት የጣና ሐይቅን የተፈጥሮ ግድብና የኢትዮጵያ የባሕል ቅርስ ግምጃቤትነት አስደርቀው በሱዳን ጠረፍ ላይ አዲስ ጣናን ለማንጣለል ተመኝተዋል።
በሰሜን አፍሪቃና መካከኛው ምሥራቅ አፍቃሪ ዴሞክራሲ ሕዝባዊ አመጽ ተቀጣጥሎ አምባገነኖችን ሁሉ ሲያሽቀነጥርና ሲያርበደብድ ወያኔዎች በገጠማቸው ከፍተኛ ሥጋትና ብርገጋ በአባይ ወንዝ ካርድ ተጠቅሞ የለውጡን ማዕበል ለመግታት የታቀደ ማደናገሪያ ስለሆነ ከመሃል አገር ርቆ ሱዳን ጠረፍ ላይ በመጀመሪያ ለመገንባት ያስጀመረው በፍጹም የወለፌንድ ሥራ ነው። ካድሬዎቹና ግብረበላዎቹ ሁሉ ዓይናቸውን በጨው አጥበው አስቀድሞ ጥናት ተደርጎ ነበር እያሉ ይቀላምዳሉ።

ለነገሩማ በአባይ ሸለቆ ላይ ጥናት የተደርገው በግብፅ የአስዋን ግድብ በሚገነባበት ወቅትና ቀጥሎም በዘመነ ደርግ ነው። በእርግጥም በቅርቡ በኖሮዊ መንግሥት ርዳታ በአባይ ወንዝ ላይ የቤካ አምቦና የመንድያ ግድብ ድጋሜ ጥናት ተጀምሮ እንደነበር ይታወቃል።

ለምን ወለፈንዲ ሆነ ቢባል በአንድ ወንዝ ላይ ጥቅመ ብዙ ግድቦች የሚሠሩት ከላይ ወደታች በቅደም ተከትል በመሆኑ ነው። በቅድሚያ በዝቅተኛው ስፍራ ሱዳን ጠረፍ ላይ ውሃው ስቲቆር በሦስትና አራት መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ሸለቆው ሁሉ በውሃ ይሞላል።

ታዲያ! እንዴት ሆኖ ነው ሌሎቹን ግድቦች በአባይ ወንዝ ላይ ለመገንባት የሚቻለው?

በግቤ ወንዝ ላይ በትክክል እንደተደረገው በአባይም ላይ የአሜሪካን መሃንዲሶች በ1957 ዓ.ም በቀየሱት ጥናት መሠረት በተቀዳሚ ጉደር ወንዝ መገናኛ አጠገብ ተገንብቶ ከሞላ በኋላ ተራ በተራ ሌሎቹ ግድቦች ይገነባሉ።

በቅርብ ዘመን በተደረገው የተሻሻለ ጥናት መሠረት ግን በመጀመሪያ አንደኛው የከራዶቢ ግድብ በሰባት ዓመት ውስጥ ተገንብቶ ሲጠናቀቅ ቀጥሎ የጠረፉ ግድብ ከዚያም ሁለተኛውና ሦስተኛው በቅደም ተከተል በረጅም እቅድና ዝግጅት እስከ 36 ዓመታት ያህል በሚወስደው የግንባታ ሂደት ከፍተኛ የኮረንቲ ኃይልና የመስኖ መሬት ማልማት ይቻላል።

ወያኔ ከጠረፍ ላይ ጀመርኩ የሚለው ለወደፊቱ ከጠረፉ ግድብ በስተቀር ሌላ አንዳችም ግድብ በአባይ ወንዝ ላይ ለምንጊዜውም መገንባት እንድሌለበት ከግብፅና ሱዳን ዋና አጋሮቹ ጋራ ውስጣዊ ስምምነት ከአላደረግ በስተቀር ሌላ አስማኝ ምክንያት የለም። በሁሉም ረገድ ተስማሚ ከሆነው የመሃል አገር ይልቅ ጠረፉ ላይ በቅድሚያ በሱዳንና ግብፅ ትብብር ለመገንባት ባላቀደም ነበር። በዚህም ሆነ ቢዚያ ባለፉት ሃያ ዓመታት ወያኔ ኢሕአዴግ ያደረገውና የሚያደረገው ቲያቲር የኢትዩጵያን ልዑላዊነትና ብሔራዊ ጥቅም የሸጠ ከአልሆነ በስተቀር ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም።

## የአባይ ሸለቆ አራቱ ታላላቅ ጥቅመ ብዙ ግድቦች እቅድ

በዘመነ አጤ ኃይለ ሥላሴ የአሜሪካን የአገር ውስጥ የመሬት መልሶ ማልማት መስሪያ ቤት ( of Reclamation, US Department of Interior, 1964, Land and water resources of Blue Nile Basin: Ethiopia) ባደረገው ቅየሳ መሠረት በአባይ ወንዝ ሸለቆ ላይ አራት ጥቅመ ብዙ ግድቦችን በመገንባት አስዋን ከሚሰጠው የኮረንቲ ኃይል ሁለት ተኩል ጊዜ የበለጠ ማመንጨትና እጅግ ብዙ የመስኖ መሬት ለማልማት እንደሚቻል አጥንተዋል። ይህ እቅድ ከሁሉም የተሻለና ተስማሚ መሆኑን በተከታታይ የተደረጉት አዲስ ጥናቶችም ያመለክታሉ። ለምሳሌ የኮሎራዶ ዩኒቨርስቲ ምሁር የተከበሩ ፖል ጄ ብሎክ ከአደረጉት ብዙ ምርምር አንዱን መጥቀስ ተገቢ ነው።

በኢትዩጵያ አባይ ሸለቆ ቅንብር የሥነ ውሃና መስኖ ማመሳሰል ድርጊያ (Paul J.Block: Integrated Management of the Blue Nile Basin in Ethiopia: Hydrology and Irrigation Modelling, May, 2007) በተሰኘ ርእስ ያቀረቡትን ያገናዝቧል።

1 የመጀመሪያው ግድብ ከጣና ሐይቅ 385 ኪሎሜትር ርቀት ላይ ጉደር ወንዝ መገናኛ አካባቢ ትልቁ የከራዶቢ ግድብ ጠቅላላ ከፍታው 252 ሜትር የሚያፈልቀው 1350ሜጋዋት ነው።

2, ሁለተኛው የመቢል ግድብ ከአንደኛው 145 ኪሎሜትር ርቀት ከብር ወንዝ መገናኛ 25 ኪሎሜትር በታች፤ ጠቅላላ ከፍታው 171 ሜትር የሚያፈልቀው 1200ሜጋዋት ይሆናል።

3, ሦስተኛው መንዲያ፣ ጠቅላላ ከፍታው 164 ሜትር የሚያፈልቀው 1620ሜጋዋት ነው።

4, አራተኛው ወደ ሱዳን ወሰን አካባቢ የጠረፍ ግድብ ጠቅላላ ከፍታው 84.5ሜትር ብቃቱም 1400 ሜጋዋት ይሆናል።

አራቱም ግድቦች ተገንብተው ሲጠናቀቁ በአጠቃላይ 5570 ሜጋዋት ከማፍለቃቸውም ሌላ ብዙ ሚሊዮን ሄክታር በመስኖ ማልማት ይቻላል። በመጀመሪያ የከረዶቢን ግድብ ለመገንባት 7 ዓመት ያህል ይወስዳል። ቀጥሎም የጠረፉ ግድብ ግንባታ ሲጠናቀቅ የመቢልና በመጨርሻም የመንደያ ገድብ ግንባታ ይጀመራል። (ያው ገጽ 6-7)

በአባይ ወንዝ ላይ በ1951 ዓ.ም በቀድሞዋ ይጎዝላቢያ መንግሥት ትብብር 11ሜጋዋት አቅም ያለው የጢስ እሳት አንደኛ ኃይል ማመንጭያ ተገነባ። አንዳችም ያካባቢ ጉዳት ሳያደርስ ስያገለግል ነበር። ቀጥሎም በዘመነ ወያኔ በእንግሊዝና ፈረንሳይ ሽርከኛ አማካሪዎች (Joint venture Coyne et Bellier, Howard Hamphreys & Rust Kennedy& Donkin) በ1989 ዓ.ም የ "ትግበራ ጥናት" አዘጋጆች ሁለተኛው የጢስ እሳት ኃይል ማመንጭያ በጣና ሐይቅ መፋሰሻ ላይ የጭያራ ጭያር መከተሪያ ግድብ ተገንብቶ ወደ ጢስ እሳት ፏፏቴ የሚፈሰውን ውሃ ሙሉ በሙሉ ጠልፎ በመውሰድ በUS$ 63 ሚሊዮን ወጪ 72ሜጋዋት የሚያፈልቅ በ1994 ዓ.ም ተጠናቆ ሥራ ጀምሮ ነበር። በዚህም ምክንያት እጅግ በጣም አስገራሚው የጢስ አባይ ፏፏቴ እንዲደርቅ የተደረገው።

<u>የአባይ ወንዝ ምስጢር</u> በሚል ርእስ የኢማክስ ( IMAX) ተባባሪ አዘጋጅ ክቡር ሪቻርድ ባንግስ በታላቅ ፀፀትና ቁጭት ዝነኛው ያባይ ፏፏቴ ተሰረቀ በማለት አገር በቀል ቢሮክራቶችና የባሕር ማዶ የፈረንሳይና እንግሊዝ መሰሪ ተባባሪዎቻቸውን የጥፋት መሳክተኛነት፤ ኢትዮጵያ ከውሃ የኤሌትሪክ ኃይል ለማግኘት የሚያስችሉ አያሌ ወንዞችና ሸለቆዎች እያሏት ከዓለም የተፈጥሮ አስደናቂዎች አንዱ የሆነውን ጢስ አባይ ለርካሽና ፈጣን ኃይል መመንጭያነት መደረጉን በአጽንኦት ኮንነውታል።

አንድም የኢትዮጵያዊ ድርጅት ወይም ግለሰብ የአባይ ፏፏቴን መሰረቅ አስመልክቶ አንዳችም ተቃውም አለመሰማቱ እጅግ በጣም ያስተዛዝባል።

ተፈጥሯዊ ፋፏቴውን የማውደም ታላቁ ሤራው በዚህ ሳያበቃ የጣኛ ሐይቅ ውሃ ተሰርስሮ የፍሰት አቅጣጭያው ተቀይሯል።

በእርግጥም በአባይ ወንዝ ላይ ከጢስ አባይ ፏፏቴ በታች እስከ ሱዳን ጠርፍ ድረስ ስንትና ስንት ለመገደቢያ ተስማሚ ሸለቆዎች መኖራቸው በአሜሪካን መሕንዲሶች ተረጋገጦ ሳለ በጢስ እሳትና ጣና ሐይቅ ላይ የተፈጸመው ሴራ ጠሳትነት ነው።

ሌሎች ብዙ ወንዞች በየቦታው እያሉን የጢስ አባይንና የጣና ሕይቅን የተፈጥሮ ሥነ ምኅዳር ሆን ተብሎ ለማቃወስ የተቀነባበረ ተንኮል ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ይባላል!!

የሴራው ዋና ተዋናያን የፈረንሳይና እንግሊዝ ኩባንያዎች ዓይናቸውን በጨው አጥበው የጢስ አባይ መድረቅ <u>አንዳችም ያካባቢ አደጋ</u> አያስከትልም ብለው የጻፉትን ይመለከቷል።

<<The study concluded that, unlike other hydropower projects with big dams, Tis Abay II would have " negligible impact on the environment, and that it would be economically very attraxtive for investment.>> ( Richard Bangs: Stealing the Nile: Famous Falls no more. http:// www.msnbc.msn.com/ id/ 3727491/ns/us_news_environment)

ባማርኛ፣

ጥናቱ እንደ ትልልቅ ግድብ ኃይል ማመንጭያ ፕሮጀክቶች ሳይሆን ጢስ አባይ ሁለተኛ ኢምንት ያካባቢ ተፅዓኖ ያሌለውና ለኢኮኖሚያዊ መዋእለ ንዋይ ፍሰት ሳቢ መሆኑን ያጠቃልላል።

በጢስ አባይ ላይ የደረሰውን ከፍተኛ ሰው ሠራሽ የአካባቢ ማቃወስ ወንጀል ከተከበሩ ሪቻርድ ባንግስ በስተቀር አንድም የምዕራባውያን ጋዜጠኛና የአካባቢ ደህንነት ጠባቂ ድርጅት ተብዬዎች ይሁኑ ግለሰቦች ተቃውሞ አላሰሙም።

የምዕራባዊ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንደ ዓለም አቀፍ ወንዞች ( International Rivers) የትላልቅ ግድቦች ያካባቢና ማኅበረ ሰባዊ አደጋ እያሉ የሚዘላብዱት ከሚያገኙት የጥቅም ግጭት አኳያ ለመሆኑ የጣና በለስና የጢስ አባይ ፕሮጀክቶች ዓይነተኛ ማረጋገጫያዎች ናቸው። ቻይና፣ ብራዚልና ሌሎች አገሮች በወንዞቻቸው ላይ ግድብ ሲገደቡ ምዕራባውያን የማጥላላት ጥሩንባቸውን ይነፋሉ። ያባይ ፏፏቴ መውደም ግን በጭራሽ ጉዳያቸው አይደልም።

ከጢስ አባይ መድረቅ ይባስ ተብሎ የጣና ሐይቅ የተፈጥሮ ግድብን ሸንቁሮ የአባይን ወንዝ ፍሳት አቅጣጫ መቀየር እንዴር ልማት ይሆናል? ሐይቁን እንደ ቻድና አለማያ ሐይቅ ለማድረቅ የተቀነባበረው ትልቁ ሤራ ለመሆኑ ከቶ አያጠራጥርም። የሚያስገርመው ነገር ሁለቱም የጢስ እሳት ኃይል ማመንጭያዎች ጣና በለስ ሲከፈት ተዘግተዋል። በተለይም በቅርቡ ስድሳ ሦስት ሚሊዩን ዶላር አስወጥቶ የተተከለው ሁለተኛው የጢስ እሳት ኃይል ማመንጭያ ምንም አገልግሎት ሳይሰጥ፣ የጣና ሐይቅ ውሃ በጠቅላላው ለበለስ ኃይል ማመንጭያነት በመወሰዱ ምክንያት ቆሞ ቀርቷል። በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው የጢስ እሳት ኃይል ማመንጭያ የተፈጥሮ ውበት የጢስ እሳት ፏፏቴ ዋና ጠንቅ መሆኑም በግልጽ እየታወቀ ስለምንስ በዚያ ስፍራ ይገነባል? የግንዛቤው ድምዳሜ የትግበራ ጥናት ተብዬውን ፍጹም መዘበራረቅና ዋጋቢስነት በግልጽ ያሳያል። ይልቁንም የፈረንሳይና እንግሊዝ አጥኚ ተብዬዎች ተልዕኮ ገንዘብ ለማገበስ ብቻ ከመሆን ሌላ ትርጉም ምንም የለውም። የጢስ እሳት ሁለተኛ ኃይል ማመንጭያ ተተክሎ ሳያገለግል ወዲያው ለመዝጋት ለምን አስቀድሞ ይገነባል? በባለሙያዎች ስሌትና ጥናት የአንድ ግድብ የአግልግሎት እድሜ ቢያንስ ከ50 እስከ መቶ ዓመት ድረስ ታስቦ ነው የሚታቀደው። የበለስ ኃይል ማመንጭያ ከሁለቱ ጢስ እሳት የበለጠ የኮረንቲ ያስገኛል ከሚል ጭፍን ግምት ይኸው የሐይቁንና ጠቅላላው የአካባቢውን ሥነ ምኅዳር ሚዛን በከፍተኛ ደረጃ የሚያቃውስ ድርጊት ተፈጽሟል። ሌላው ማደናቆሪያ የጣና በለስ ፍሳሽ ለመስኖ ይውላል ተብሏል። የበለስ ወንዝ ቢገደብ ኖሮ ኮረንቲና ሰፊ የመስኖ መሬት አይሰጥም ያለው ማነው? የጣና በለስ ኃይል ማመንጨት የሚችለው የጣና ሐይቅ ውሃ ተሟጦ እስኪያልቅ ድረስ ብቻ ነው። ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ሐይቁ በቂ ውሃ ማከማቸት የሚችለው በክረምቱ ወራት ብቻ ነው። ስለሆነም የጣና በለስ ኃይል ማመንጭያ ለጠቅላላው አካባቢ ከፍተኛ መቅሰፍት ያመጣል። ሐይቁ የአካባቢው ሕዝብ የመጠጥ ውሃና የሕይወት ምንጭ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

የጢስ እሳት ፏፏቴ የአባይ ወንዝ ግርማ ሞገስ በበለስ ምክንያት መሰረቅ የለበትም። ለሁለተኛው የጢስ እሳት ኃይል ማመንጭያ ግንባታ የወጣው መዋእለ ንዋይና ጉልበት ኪሳራ ነው። ለጣና በለስና ለጢስ አባይ ሁለተኛ የወጣው ገንዘብ በአባይ ወንዝ ሸለቆ ከፏፏቴ በታች ትልቅ ግድብ ያስተክል ነበር። የጣና በለስ ፕሮጄክት ከጥቅሙ የሚያስከትለው ጉዳት ያመዝናል።

የሐይቁን ሥነ ምኅዳር ፈጽሞ ያላገናዘበ ያካባቢውን ሕዝብ ፍላጎትና ስምምነት በጭራሽ ያለገኘ አድጋ ነው።

በአባይ ወንዝ ከፏፏቴው በታች ባለው ሸለቆ ግድብ ሳለመሥራት ታስቦ የጣና ሐይቅ የተፈጥሮ ማጠራቀሚያና ጢስ አባይ የሚበላሹት ለማን ተብሎ ነው?

የጣና በለስ ኃይል ማመንጭያ በሚያስከትለው ከፍተኛ ውሃዊና ሥነ ምኅዳራዊ አደጋ ምክንያት በአስችኳይ መዘጋት አለበት። የአባይ ወንዝ በተፈጥሮ መፉሰሻው በጢስ እሳት ላይ መፍሰስ ይኖርበታል።

አስቀድሞ በተጠናው እቅድ መሠረት አራቱ ታላላቅ ግድቦች ተራ በተራ ቢገነቡ ኖሮ ከጣና በለስ ኃይል ማንጭያ 12 ጊዜ በለጠ የኤሌክትሪክ ጉልበትና ብዙ ሚሊዎን ጋሻ የመስኖ መሬት ጥቅም ላይ ውሎ የገበሬው ኑሮ በተሻሻለ ነበር።

የአባይ ወንዝ ሸለቆ የተፈጥሮ ሃብትን መጠቀም የኢትዮጵያውያን ብቸኛ ውሳኔ ነው።
ለመሆኑ አሜሪካ የሜክሲኮን ፈቃድ ጠይቃ አይደለም ታላቅ ግድብ የገነባችው፤ ቱርክ የሶሪያና የኢራቅን ፈቃድ አልጠየቀችም። በአፍሪቃም ታንዛኒያ ከቪክቶሪያ ሐይቅ በራሷ ብቸኛ ፈቃድ በቂ ውሃ ወስዳ ለሕዝባ ጥቅም አውላለች። በኢትዮጵያ ብቻ ነው ዘወትር የምግብ ልመና አባዜ ሥር የሰደደው። ከመለመን መልስ በአንድ በኩል ግብፅን ለማስደሰት እየተባለ በአባይና ጣና ሐይቅ ላይ ከጥፋት ሌላ ትክክለኛ ልማት አልተደረገም። በሌላ በኩል ደግሞ የይስሙላ የአባይ ወንዝ ዐቃቢና ተከላካይ መስሎ ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋራ ወያኔ ኢሕአዴግ እየተሞዳሞደ ሰፋፊ ለም መሬቶችን ከጋምቤላ እስከ ሁመራ ድረስ ገጸ በረከት አድርጎ የሚሰጠው።
የጣባብ ጎሠኞችና ፀረ ኢትዮጵያ ምልምሎች ጥርቅም ወያኔ የተሰኘው ስብስብ የተከዜን ወንዝ ግድብ በቅድሚያ በኢትዮጵያ ኪሳራ ያስገነባው "ለታላቋ ትግራይ ትግርኝ ሪፑብሊክ" ኃይል ማመንጭያ ታስቦ ያለምንም ሳይንሳዊ ጥናት፣ በዐማራ ሕዝብ ጭፍን ጥላቻና ምቀኝነት የኢትዮጵያን አባይን ወንዝ ለግብፅ ጥቅም አሳልፎ በማበርከት ሲሞዳሞድ ቆይቶ ከአለፍ አገደም የይስሙላ ጩኸት ያንባርቃል። በተከዜ ላይ የተገነባው ግድብ ከፍታው 185 ሜትር ሲሆን ኃይል የማፍለቅ አቅሙ 300ሜጋዋት ነው ተብሎ ሲዘመር ዛሬ ግን በተግባር የሚሰጠው ጥቅም ሲሦውን ብቻ ነው። በጠረፍ ላይ ይገነባል የሚባለውም አንድ ግድብ ብቻውን የተባለውን 5250 ሜጋዋት ማፍለቅ በጭራሽ አይችልም። የተባለው አቅም የፕሮፓጋንዳ ማጣፈጭያ ብቻ ነው።
ወያኔ ኢሕአዴግና ሻዕቢያ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሃብት ዝርፊያ ላይ ጦር ተማዘው ብዙ ሕይወትና ንብረት ወደሚል። ወያኔ እስከ ቅርብ ወራት ድረስ በአባይ ሸለቆ አንድም እንኳ ግድብ ላለመሥራት የጌቶችን ትዕዛዝና ፍላጎት ለመፈጸም ብቻ ደፋ ቀና ሲል ስንብቶ ይልቁንም የጢስ አባይንና የጣና ሐይቅን የተፈጥሮ ግድብ በማስጥፋት ያካባቢውን ዋና የቱሪስት እንዱስትሪና የሕልውና ዋስትና ለአደጋ ዳርጎ ዛሬ ደግሞ የሕዳሴ ግድብ ሱዳን ወሰን ላይ ለመሥራት ተነስቻለሁ እያለ ያደናግራል። የጣና ሐይቅን እንደ ዓለማያ አስደርቆ ሱዳን ጠርፍ ላይ እጥፉን እሠራላችኋለሁ እያለ ይለፍፋል። መሃይማንና ሆድአደር ቅጥሮኝች የኢትዮጵያ የተፈጥሮና የባሕል ቅርሶች ሲወድሙ ከወያኔ ጋራ ወግነው ያሸቃብጣሉ።

## ያለም ባንክ

የጣና በለስ ፕሮጄክት የተደገፈው በዓለም ባንክ ሲሆን (Tana & Beles Integrated Water Resources Development Project. Report .No. 43400-ET. May, 2008) የወያኔ ባለሚሎች ግን በኢትዮጵያ መንግሥት ወጪ ነው እያሉ ያወናብዳሉ። በተጥቀሰው ዘገባ መሠረት ባንኩ ለፕሮጄክቱ ይሁንታ የፈቀደው በቅድሚያ የሱዳንና ግብፅን መልካም ፈቃድ በጽሑፍ ከአገኘ በኋላ ነው። እንዴታ! ለምን አይፈቅዱ? የአባይ ወንዝ በዙሪያ ጥምጥም ከ800 ኪሎሜትር በላይ የሆነውን ርቀት በአቋራጭ በበለስ ወንዝ በኩል ፈጥኖ ሲደርስላቸው። ባንኩ ስለ የተፈጥሮ አካባቢ ሰው ሠራሽ ብክለትና አደጋ እጨነቃለሁ እያለ በሰፊው ይቀላምዳል። እንዲያውም ከ10 ሜትር በላይ ከፍታ ላላቸው ግድቦች ግንባታ መዋእለ ንዋይ አላበድርም፣ አልተባበርም ይላል። ታዲያ ባንኩ የጣና ሐይቅን ተከንባይ ሥነ ምኅዳር ላይ የሚደርሰውን አደጋ በግልጽ አውቆ የውሃው ፍሰት አቅጣጭያ ተቀይሮ በጢስ አባይና ጣና ኪሳራ ለተባሉት አገሮች ዘላቂ ጠቀሜታ ለማረጋገጥ የተደረገ ተንኮል ነው። በመሆኑም የዓለም ባንክ የአራቱን ግድቦች የግንባታ እቅድ ተቃውሞ ለጣና በለስ ፕሮጄክት ተባባሪ የሆነው የተለመደውን የግብፅን ጩኸት ሰምቶና ተባብሮ ነው።

ከናይል ወንዝ ውሃ 85% የሚሆነው ከአባይ ወንዝ ከኢትዮጵያ ይገኛል። እስከ ዛሬ ድረስ ግብፅና ሱዳን የናይልን ወንዝ ብቸኛ ባሌቤትና ተጠቃሚ ሆነው ቆይተዋል። ይህም ሆኖ እያለ ግብፅና ሱዳን አጉራሹን ነካሽ እንዲሉ ዘወትር ፀረ ኢትዮጵያ ሴራና ወረራ ከማድረግ አልተቆጠቡም። ዘወተር የኢትይጵያን ሕዝብና መንግሥት በማዳከም የአባይን ወንዝ ለብቻቸው ለመጠቀም ፍላጎታቸው ነው። ከዘገባው በተጨማሪ የምንረዳው ባንኩና ለጋሽ ተብዬ አገሮችና ድርጅቶች በጣና ሐይቅ አካባቢ መጋቢ ወንዞች ላይ ግድብ ለመሥራት እንዳቀዱ ተገልጿል። በዚህም መሠረት በጣና ሐይቅ አካባቢ "አስከፊ ድህነትን" ለመዋጋት እያሉ በሰፊው ለፍፈዋል።
ድንቄም ድህነት!! እረ ለመሆኑ የጎጃም ገበሬ አይደለም እንዴ ዝንተ ዓላም ጥቅመ ቢስ የከተማ ውዝፍ ተቀላቢዎችንና አቀባባይ ከበርቴዎችን የሚመግበው?
ለማያውቁሽ ታጠኝ እንዲሉ የዓለም ባንክና አይኤምኤፍ ( IMF) በዓለም ላይ በተለይም በአፍሪቃና ላቲን አሜሪካ የመዋቅር ማስተካከል ( Structural Adjustment Programme , SAP) በተባለው መርሃ ግብር ርሃብና ድህነትን እጅግ በጣም አባባሽና አስፋፊዎች መሆናቸው ሐቅ ነው።
በኢትዮጵያ ወታደራዊ ደርግ ከወደቀ ማግስትና የባንቱስታን አፓርታይድ የዘር ፓለቲካ ከሰፈነበት ጀምሮ ደርግ ከሕዝቡ ያለአግባብ የወረሰው ርስታና ንብረት ለምዕራብ መንግሥታትና ኩባንያዎቻቸው በነፃ ገበያ ሽፋን የኢትዮጵያን ሰፊ ድንግል መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ለመዝረፍ ሁኔታው ተመቻችቷል።

በጣና ሐይቅ ዳርቻ 700 ሄክታር መሬት ለአበባ ለአውሮፓ የጣሊያናን ሆላንድ የውጭ ንግድ ማሳደጊያ የግል ከበርቴዎች ተመድቧል። ይህም ሌላው ተጨማሪ የጠና ሐይቅ አድጋ ነው። መቼም ያበባ ተከላ ምርት ያለ ፀረ ተባይና ፀረ አረም ኬሚካል መጠቀም ከቶ አይታሰብም። የኬሚካል ማዳበሪያና ፀረ ተባይ ውዳቂ ፍሳሽ ወደ ወንዞችና ሐይቆች ውስጥ ሲገቡ በሰውና እንስሳት ላይ የሚያደርሱት ጠንቅ ከፍተኛ ነው። በመጠጥ ውሃ ምንጮች፣ ወንዞችና ሐይቆች አካባቢ በሚገኙ ማሳዎች ላይ ከፍግና ብስባሽ በስተቀር ኬሚካላዊ ማዳበሪያና ፀረ ተባይ መጠቀም በሕግ የተከለከለ መሆን ነበረበት። በተጨማሪም የቤት ውስጥና የባሕርዳር እንዱስትሪዎች ቆሻሻ ፍሳሽ ሳይጣሩ ወደ ሐይቁ መግባት አልነበረባቸውም።
በተመሳሳይ ሁኔታ በአዲስ አበባ ዙሪያ እስከ አዋስ ድረስ ለም ሰፋፊ የሰብል ማሳዎች ከገበሬው ተቀምተው ለሆላንድ ከበርቴዎች ያበባ ማሳደጊያ በተደረጉበት አካባቢዎችና ይልቁንም በወንጂ የቆዳ ፋብሪካ ኬሚካል ውዳቂ ፍሳሽ በሰው ሕይወትና እንስሳት ላይ እያስከተሉ ያለውን በሽታና ጉዳት ያጤኗል።

## <u>በአንድ ራስ ሁለት ምላስ</u>

በዘመን ደርግ የተጀመረው የግልገል ግቤ ኃይል ማመንጭያ በጥሩ ሁኔታ እየተገነባ ነው። የተገነቡትና ለመገንባት በእቅድ ላይ ያሉት ሲጠናቁ ጠቅላላ (ከግቤ አንድ እስከ አምስት) የኮረንቲ ኃይል የማመንጨት አቅማቸው እስከ 4506 ሜጋ ዋት ይደርሳል። የተከዜንና የጣና በለስን ባንድነት በደመሩ የሚገኘው ውጤት 5266 ሜጋዋት ይሆናል። ይህም በአባይ ወንዝ ሸለቆ ላይ ከታቀዱት 4 ጥቅመ ብዙ ግድቦች ለማፍለቅ ከሚችሉት 5570 ሜጋዋት ያነሰ ነው። በተከዜ ይሁን በግልገል ግቤ ግድቦች በመስኖ ሊለማ የሚቻለው መሬት ከአባይ ሸለቆ ጋራ ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ ነው።

የአራቱ ጥቅመ ብዙ ግድቦች በኢትዮጵያ መገንባት ለሱዳንም ከፍተኛ ጥቀሜታ ይኖረዋል። በዚያም በመስኖ የሚለማው መሬት 5.5% እንደሚጨምር የተደረጉት ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ከሁሉም በላይ የአራቱ ጥቅመ ብዙ ግድቦች በኢትዮጵያ መገንባት በታችኛው ተፋሳሽ አገሮች ላይ አንዳችም ጉዳት አያስከትልም።

በአስዋን በርሃም ስፍራ ላይ ብላሽ ሆኖ በየዓመቱ የሚባክነው 2.5 ቢሊዎን ኩባዊ ሜትር ውሃን ከትነት ያስቀራል እንጂ። ይህን በተመለከተ ኪው ጎርና ሌሎች በምሥራቅ አባይ ወንዝ ሸለቆ የጥቅመ ብዙ ብዙ ግድብ ቅንባሮት ተስማሚ ክዋኖት ( Q.Goor et al Optimal operation of amultipurpose multiresevoir System in the eastern Nile River Basin. Hydro and Earth Syst. Sci. Disc. 7, 4331-4368, 2010) በተባለ ርእስ ያቀረቡትን ጥናት ያገናዝቧል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘወትር በድርቅና ሰው ሠራሽ ችጋር ሽፋን ዝንተ ዓለም ተመጽዋችና ለማኝ፣ ተስፋቢስ ጥገኛ ሽቀጥ ማራገፊያ ሆኖ የተፈጥሮ ሃብቱን እንዳይጠቅም የሚፈልጉ አገር በቀልና የሩቅ ጠላቶች አሉ። በዓለም ላይ "የኢትዮጵያ ችጋር" ሥነ ልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሚታ አስገኝቷል። በችጋር ስም እየለመኑ ትርፍ ያካባቱ፣ የቅንጦት ኑሯቸውን የሚቀጩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ስፍር ቁጥር የላቸውም። በመሆኑም ችጋር እንዲስፋፉ እንጂ እንዲጠፉ እአይፈለግም። ችጋሩ ከሰሜንና ደቡብ ምሥራቅ ወደ ደቡብና ምዕራብ ለምለም አካባቢዎች ተዟምቷል። አረንጓዴ ችጋር ይሉታል። የደቡብ ምዕራብ ለም መሬት ለሕንዶችና ለአረቦች፣ ለጀርመኖች፣ ለሆላንዶች ወዘተረፈ ለ99 ዓመት በርካሽ ተቸብችቧል።

እራሳቸውን የምዕራብ መንግሥታዊ ያልሆን ባይ ድርጅቶች እንደ ዓለም አቀፍ ወንዞች ( INTERNATIONAL RIVERS, SURVIVAL INTERNATIONAL etc) ለምን በኦሞ ወንዝ ላይ የግልገል ግቤ ኃይል ማምንጭያዎች በተለይም ግልገል ግቤ ሦስት ይገነባል ብለው እንበለ እፍረት ያናፋሉ። ለምሳሌ እንቶኒ ሚቸል የተባለው አወናባጅ ቅጥረኛ (http://www.Anthonymichel.com) ለምን የግልገል ግቤ ፫ተኛ ይገነባል ብሎ ያዞ እንባ ያለቅሳል። ለኦሞ አካባቢ ነባር ጎሣዎች እራሱን በራሱ ጠበቃ አስመስሎ ይቀባጥራል። ሌሎችም እንዲሁ የግልገል ግቤ ግድቦች በቱርካና ሐይቅ ላይ የተፈጥሮ አደጋ ያስከትላል እያሉ ለቱርካና ሕዝብ ቅቤ አንጓችና የበላይ ጠባቂ ፀረ ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ ይነዛሉ። በኦሞ ወንዝ ላይ ግድብ ተሠርቶ ኃይል ማምንጨት በቱርካና ሐይቅ ላይ የአካባቢ መቃወስ አደጋ ያስከትላል እያሉ ሲዛንባርቁ የጣና ሐይቅ መሸንቆርና የውሃው ፍስተ አቅጣጭያ መቀየርና የጢስ አባይ መድረቅ በአካባቢው ሥነ ምኅዳር ላይ ተፅዕኖ የለውም። የጣና በለስ ፕሮጄክት ለሚያስከትለው ተጨባጪ ያካባቢ አደጋ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለዋል። ለእነዚህ የቀበሮ ባሕታውያን የጣና ሐይቅ ሥነ ምኅዳራዊ ቀውስ ጉዳያቸው አይደለም።

እንዲያውም የእንግሊዝና የፈረንሳይ የትግብርት ጥናት አቀናባሪ ባለሙያ ተብዬ ነጋዴዎች ዘንድ ፕሮጀክቱ ለግል ከበርቴዎች መዋእለ ንዋይ ማዋል የሚያመች ነው ይባላል።

ምዕራባውያን ባለሁለት ምላሶችና አፈቀላጤያቸው የእንግሊዞች የወሬ መኪና ቢቢሲ ከኬኒያ መንግሥት ይበልጥ ለቱርካናዎች አሳቢ መስሎ በግልገል ግቤ ሦስተኛ ግድብ ግንባታ ላይ ውዥንብር ይነዛል። ቢቢሲና ብጤዎቹ ዘወትር ባለፈው ጊዜ በችጋር ጣር ላይ ያሉ ሕፃናትና አዛውንትን ፎቶ ግራፍ ካላሳዩ ፈጽሞ ርካታ አያገኙም።

በሌላ በኩል የእንግሊዝ መንግሥትና ተባባሪዎች ሁሉ የወያኔ ቅጥረኛና አሽንጓሊት የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ ዋና ደጋፊና ተንከባካቢ ናቸው። የወያኔ አሕአዴግ ፖሊስና ሰላይ ጆሌዎች ሁሉ የሚሠለጥኑት፣ ትጥቅና ዝግጅት የሚቀርብላቸው በእንግሊዞች ነው።

ግራዋ ሳሙኤል

የሥነ ውሃና ሥነ ምድር መሐንዲስ